AM



አለም አቀፍ ጥበቃ የሚ ጠይቁ ሕጻናት

መረጃ ብቻቸውን ለሚመጡ አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ሕጻናት፣
የድንጋጌ (EU) ቁጥር 604/2013 አንቀጽ 4

ይህን ወረቀት የሰጠናችሁ ጥበቃ እንደምትፈልጉ ስለገለፃችሁና ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች እንደሆነ ስለነገራችሁን ነው። ዕድሜያችሁ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ ህጻን ተብላችሁ ትጠራላችሁ። ሠራተኞቹ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ብለው ሊጠሯችሁም ይችላል ይሄም ሕጻን ከሚለው ጋር አንድ ነው። ሠራተኞቹ ማለት ለጥበቃ ያቀረባችሁትን ጥያቄ ላይ ውሳኔ የሚሰጡት ሰዎች ናቸው።

እዚህ ጥበቃ ስፈለጋችሁ በትውልድ አገራችሁ ፈርታችሁ ከሆነ ይህንን 'ጥገኝነት' እንለዋለን፡ ፡ መጠለያ ማለት ጥበቃ እና ደህንነት የሚሰጥ ቦታ ነው።


ለሠራተኞቹ መደበኛ የጥገኝነት ጥያቄ ስታቀርቡ ህጉ ይሄን 'አለም አቀፍ ጥበቃ የመጠየቂያ ማመልከቻ' ይለዋል። ጥበቃ የሚጠይቀው ሰው 'አመልካች' ይባላል። አንዳንድ ጊዜም ሰዎች 'ጥገኝነት ፈላጊ' ብለው ሲጠሯችሁ ልትሰሙ ትችላላችሁ።

ወላጆቻችሁ ከእናንተ ጋር መሆን አለባቸው፣ ካልሆኑ ግን ወይም ወደዚህ ስትመጡ ተለያይታችሁ ከሆነ **'ብቻውን የመጣ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ'** ተብላችሁ ትጠራላችሁ።

እንደዚህ ከሆነ፣ በሂደቱ ላይ የሚረዳችሁ ትልቅ ሰው 'ተወካይ' እንመድብላችኋለን፡ ፡ ማመለከቻችሁን አስመልክቶ የሚረዳችሁ ወይም የምትረዳችሁ ሲሆን ሠራተኞቹን ማናገር ሲኖርባችሁም አብሯችሁ ሊሆን/ልትሆን ይችላል/ትችላለች። ስለ ችግራችሁና ስለ ፍርሀታችሁ ከተወካያችሁ ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። የተወካያችሁ ስራ የእናንተ ጥቅሞች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ማድረግ ነው፣ ይሄም ማለት ፍላጎታችሁ፣ ደህንነታችሁ፣ ጤንነታችሁ፣ ማሕበራዊ ዕድገታችሁና አስተያየቶቻችሁ ከግምት ውስጥ ይገባሉ ማለት ነው። በተጨማሪም ተወካያችሁ ከቤተሰብ ጋር መልሶ የመቀላቀል ዕድሎችንም ይሠራል/ትሠራለች.

ይህ ወረቀት ለመረጃ አገልግሎት ብቻ ይውላል። አላማውም የ ዱብሊን አሠራን አስመልክቶ ለአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች አስፈላጊ መረጃዎችን መስጠት ነው። በራሱ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን አይፈጥርም/አያስከትልም። በዱብሊን አሠራር ስር ያሉ መንግስታትና ሰዎች መብቶቹ እና ግዴታዎቹ በድንጋጌው (EU) 604/2013 ውስጥ የተካተቱት ናቸው።

©የአውሮፓ ሕብረት 2014
መልሶ ማተም ይፈቀዳል። እያንዳዱን ፎቶ ለማንኛውም አገልግሎት ለመጠቀምም ሆነ እንደገና ለማተም፣ ከኮፒ ራይቱ ባለቤቶች በቀጥታ ፈቃድ ሊሰጥ ይገባል።



የዱብሊን አገሮች 28ቱን የአውሮፓ ሕብረት አገሮች ያካትታል (ኦስትሪያ (AT), ቤልጂየም (BE), ቡልጋሪያ (BG), ክሮሺያ (HR), ሳይፕረስ (CY), ቼክ ሪፓብሊክ (CZ), ዴንማርክ (DK), ኢስቶኒያ (ET), ፊንላድ (FI), ፈረንሳይ (FR), ጀርመን (DE), ግሪክ (EL), ሀንጋሪ (HU), አየርላድ (IE), ጣሊያን (IT), ላቲቪያ (LV), ሊቱኒያ (LT), ሉክሰምበርግ (LU), ማልታ (MT), ኔዘርላንድስ (NL), ፖላንድ (PL), ፖርቹጋል (PT), ሮማኒያ (RO), ስሎቫኪ (SK), ስሎቬኒያ (SI), ስፔን (ES), ስዊድን (SE), ዩናይትድ ኪንግደም (UK)) እንዲሁም ከዱብሊን ድንጋጌ ጋር "የተቆራኙ" 4 አገሮች (ኖርዌይ (NO), አይስላንድ (IS), ስዊዘርላንድ (CH) እና ሊችቴንስቴይን (LI))



©European Union

ያልገባችሁ ነገር ካለ፣ ተወካያችሁን ወይም የእኛን ሠራተኞች በመጠየቅ እርዳታ ማግኘት ትችላላችሁ!

ምንም እንኳ በዚህ አገር ላይ ጥገኝነት ብትጠይቁ፣ ጥያቄያችሁን ተቀብሎ የሚያየው ሌላ አገር ሊሆን ይችላል።

የጥበቃ ጥያቄያችሁን ለመመርመር ሀላፊነት የሚወስደው አንድ አገር ብቻ ነው። ይሄም የ **"ዱብሊን ድንጋጌ"** በተባለ ሕግ ተወስኗል። ጥያቄያችሁን በሀላፊነት የምንመረምረው እኛ መሆናችንን ወይም ደግሞ ሌላ አገር መሆኑን እንድንወስን ይሄ ሕግ ያስገድደናል -- ይሄንንም "የዱብሊን አሠራር" እንለዋለን።

ይህ ሕግ 32 አገሮችን በሚያካትት የመልክአ ምድራዊ ቀጠና ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል[1]፡ ፡ ለዚህ ወረቀት ሲባል፣ እነኚህን 32 አገሮች "የዱብሊን አገሮች" ብለን እንጠራቸዋለን።

ከሠራተኞቹ ጠፍታችሁ አትሂዱ ወደ ሌላ የዱብሊን አገርም አትሸሹ። አንዳድ ሰዎች እደዚያ ማድረግ ጥሩ እደሆነ ሊመክሯችሁ ይችላሉ። የሆነ ሰው እንድትሸሹ ወይም ከእነሱ ጋር እንድትሄዱ ከነገራችሁ፣ ወዲያውኑ ለተወካያችሁ ወይም ለመንግስት ሠራተኞች ተናገሩ።

ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከሆነ እባካችሁ ወዲያውኑ ለመንግስት ሠራተኞቹ ተናገሩ:

- ብቻችሁን ሆናችሁ እናታችሁ፣ አባታችሁ፣ ወንድም ወይም እህታችሁ፣ አክስታችሁ [2]፣ አጎታችሁ [3]፣ ሴት አያታችሁ ወይም ወንድ አያታችሁ በገጽ 3 በሚገኙ ከ32ቱ የዱብሊን አገሮች በአንዱ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ ብላችሁ ካሰባችሁ
- እንደዚያ ከሆነ፣ ከእነሱ ጋር መኖር መፈለግ አለመፈለጋችሁን፣
- ከሌላ ሰው ጋር ወደዚያ አገር መሄድ ትፈልጉ ከሆነ ከማን ጋር መሄድ እንደምትፈልጉ፣
- ከተዘረዘሩት 32 የ"ዱብሊን አገሮች" ወደ ሌላኛው ከዚህ በፊት ሄዳችሁ የምታውቁ ከሆነ፣
- የጣት አሻራችሁ በሌላ የዱብሊን አገር ተወስዶ ከሆነ፣ የጣት አሻራ ማለት እናንተን ለመለየት የሚጠቅም ከጣቶቻችሁ የሚወሰድ ምስል ነው፣
- በሌላ የዱብሊን አገር የጥገኝነት ማመልከቻ አስገብታችሁ ከሆነ።

ከመንግስት ሠራተኞቹ ጋር መተባበርና ለእሱም እውነቱን መናገር በጣም ጠቃሚ ነው።

ለጥበቃ ስታመለክቱ ወላጅ አብሯችሁ ከሌለ የዱብሊን ስርዓት ሊረዳችሁ ይችላል።

ስለእነሱ በቂ መረጃ ካለን፣ ወላጆቻችሁን ወይም ዘመዶቻችሁን በዱብሊን አገሮች ውስጥ እንፈልጋቸዋለን። ካገኘናቸው፣ ወላጆቻችሁ ወይም ዘመዶቻችሁ በሚኖሩበት አገር እንድትገናኙ ለማድረግ እሞክራለን። ከዚም ያኛው አገር የጥበቃ ጥያቄያችሁን ለመመርር ሀላፊነቱን ይወስዳል።

---

1) **በገጽ 3 ላይ የዚህን አካባቢ ካርታ ታገኛላችሁ።**
2) **የእናታችሁ እህት ወይም የአባታችሁ እህት**
3) **የእናታችሁ ወንድም ወይም የአባታችሁ ወንድም**

ብቻችሁን ከሆናችሁና በሌላ የዱብሊን አገር ቤተሰብ ወይም ዘመድ ከሌላችሁ፣ ማመልከቻችሁ እዚሁ አገር ሊመረመር የሚችልበት ዕድሉ የሰፋ ነው።

ምንም እንኳ ሕጉ ሀላፊነቱን ለሌላ አገር ቢሰጥም፣ ማመልከቻችሁን እዚህ አገር ለመመርር ልንመርጥ እንችላለን። ይሄንንም ለሰብዓዊ፣ ለቤተሰብ ወይም ባሕላዊ ምክንያቶች ስንል ልናደርገው እንችላለን።

በዚህ ሂደት ውስጥ፣ **የእናንተን ጥቅም ለማስጠበቅ ሁሌም እንሞክራለን**፣ ሰብዓዊ መብቶቻችሁ ሊጣሱ ወደሚችሉበት አገርም አንልካችሁም።

የእናንተን ጥቅም ለማስጠበቅ ሁሌም እንሞክራለን ማለት ምን ማለት ነው? ይሄም ማለት እኛ፡

- ከቤተሰባችሁ ጋር በአንድ አገር መሆን እደምትችሉ እናረጋግጣለን፣
- በተለይም በመጥፎ ሁኔታ ሊይዟችሁ ከሚፈልጉ/ ሊጎዷችሁ ከሚፈልኩ ሰዎች የመዳንና የመጠበቅ ስሜት እንዲሰማችሁ እናደርጋለን፤
- በደህና እና በጤናማ ሁኔታ እንደምታድጉ፣ ምግብና መጠለያ እንደምታገኙ እንዲሁም የማሕራዊ ዕድገት ፍላጎቶቻችሁም መሟላታቸውን እናረጋግጣለን፣
- አስተሳሰባችሁን ከግምት ውስጥ እናስገባለን፣ ለምሳሌ ከዘመድ ጋር መቆየት ትፈልጋላችሁ ወይስ አትፈልጉም የሚለውን።



©European Union

ዕድሜያችሁ

ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች “ትልቅ ሰዎች” ናቸው። ከሕጻናትና ታዳጊዎች (“ለአቅመ አዳም ያልደረሱ”) በተለየ ሁኔታ ይያዛሉ።

እባካችሁ ስለ ዕድሜያችሁ ትክክለኛ መረጃ ስጡ።

ዕድሜያችሁን የሚያሳይ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ካላችሁ ለሠራተኞቹ አሳዩ። ሠራተኞቹ ዕድሜያችሁ ላይ ጥያቄ ካነሱ፣ ከ18 ዓመት በላይ ወይም በታች መሆናችሁን ለማረጋገጥ ዶክተር እንዲያችሁ ሊደረጉ ይችላል። ማንኛውም የሕክምና ምርመራ ከመደረጉ በፊት እናንተና ወኪላችሁ በዚህ ላይ መስማማት አለባችሁ።

በሚቀጥሉት መስመሮች የዱብሊን አሠራር እንዴት ሊረዳችሁ እንደሚችልና ምን ይፈጠራል ብላችሁ መጠበቅ እንደሚኖርባችሁ ሊኖሯችሁ የሚችሉትን የተለመዱ ጥያቄዎች ለመመለስ እሞክራለን፡፡

የጣት አሻራ -- ምንድን ነው? ለምንድን ነው የሚወሰደው?

ጥገኝነት ስትጠይቁ ዕድሜያችሁ 14 እና ከዚያ በላይ ከሆነ፣ የጣቶቻችሁ ምስል (“የጣት አሻራ” የሚባለው) ተነስቶ የጣት አሻራ ወደሚያከማቸው “ዩሮዳክ” ወደተባለ የመረጃ ቋት ይላካል፡፡ በዚህ ሂደት ላይ ተባባሪ መሆን አለባችሁ -- ለጥገኝነት የሚመለከቱ ሰዎች ሁሉ የጣት አሻራ እንዲሰጡ በሕግ ይገደዳሉ፡፡

ከዚህ በፊት ለጥገኝነት አመልክታችሁ እንደነበር ለማረጋገጥ ወይም ከዚህ በፊት ድንበር ላይ የጣት አሻራ ሰጥታችሁ ከሆነ የሆነ ጊዜ ላይ የጣት አሻራችሁ ታይቶ ሊረጋገጥ ይችላል፡ ፡ በሌላ የዱብሊን አገር የጥገኝነት ማመልከቻ አቅርባችሁ መሆኑ ከተደረሰበትና መሄድ ከፈለጋችሁ ወደዚያ አገር እንድትሄዱ ትደረጋላችሁ፡፡ ከዚያም ያ አገር ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያስገባችሁትን ጥያቄ ለመመርመር ሀላፊነቱን ይወስዳል፡፡

የጣት አሻራችሁ ለ10 ዓመት ይቀመጣል፡፡ ከ10 ዓመት በኋላ ከመረጃ ቋቱ በራሱ ይሰረዛል፡ ፡ ለጥበቃ ያስገባችሁት ጥያቄ ከተሳካላችሁ፣ የጣት አሻራችሁ በራሱ ጊዜ እስኪሰረዝ ድረስ በመረጃ ቋቱ ይቆያል፡፡ በሌላ ጊዜ የዱብሊን አገር ዜጋ ከሆናችሁ የጣት አሻራችሁ ይሰረዛል፡፡ ዩሮዳክ ውስጥ የሚቀመጠው የጣት አሻራችሁና ጾታችሁ ብቻ ነው -- ስማችሁ፣ ፎቷችሁ፣ የትውልድ ቀናችሁ እና ዜግነታችሁ ወደ መረጃ ቋቱ አይላክም ወይ አይቀመጡም፡፡ ሆኖም አነኚህ ዝርዝሮች በብሔራዊ የመረጃ ቋታችን ሊቀመጡ ይችላሉ፡ ፡ በዩሮዳክ ውስጥ የሚቀመጠው መረጃ ከዱብሊን አገሮች ውጭ ከሆነ ለሌላ አገር ወይም ድርጅት አይሰጡም፡፡



ከጁላይ 20፣ 2015 ጀምሮ፣ የጣት አሻራችሁ ከባድ ወንጀሎችና ሽብርተኝነትን ለመከላከል፣ ለማግኘትና ለመመርመር ጉዳዮች የዩሮዳክ የመረጃ ቋትን መጠቀም እንዲችሉ እንዲፈቀድላቸው ጥያቄ በሚያቀርቡ ፖሊስና የአውሮፓ ፖሊስ ቢሮ (ዩሮፖል)ን በመሳሰሉ ድርጅቶች ሊፈተሽ ይችላል፡፡



©European Union

የመንግስት ሠራተኞቹ ስለእናንተ ሁኔታ ማወቅ እንዳለባችሁ ማረጋገጥ የሚኖርባችሁ ምንድን ነው?

የጥገኝነት ጥያቄያችሁን በሀላፊነት የሚመረምረው የትኛው አገር እንደሆነ ለመወሰን እንዲቻል ቃለ መጠይቅ ልትደረጉ ትችላላችሁ (የግል ቃለ መጠይቅ)፡፡ በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ፣ ‘የዱብሊን አሠራር’ ምን እንደሆነ የእኛ የመንግስት ሠራተኞች ያብራሩላችኋል በተጨማሪም እናንተን ከቤተሰባችሁ ጋር በሌላ የዱብሊን አገር መልሶ ማቀላቀል የሚቻ ከሆነ ይሞክራሉ፡፡

ወላጆቻችሁ፣ እህት/ወንድሞቻችሁ ወይም ዘመዶቻችሁ በሌላ የዱብሊን አገር ውስጥ እንደሚኖሩ ካወቃችሁ፣ እባካችሁ ይሄን ቃለ መጠይቅ ለሚያደርጋችሁ ሰው መናገር እንዳትረሱ፡፡ ቤተሰባችሁን ለማግኘት እንዲጠቅመን እባካችሁ በተቻለ መጠን ብዙ መረጃ ስጡ - ስሞች፣ አድራሻዎችን፣ የስልክ ቁጥሮችን ወዘተ፡፡

በቃለ መጠይቁ፣ ከዚህ በፊት ወደ ሌላ የዱብሊን አገር ሄዳችሁ ታውቁ እንደነበር ልትጠየቁ ትችላችሁ። እባካችሁ እውነቱን ተናገሩ።

ወደ ቃለ መጠይቅ ስትትገቡ ወኪላችሁ እርዳታና ድጋፍ ሊያደርግላችሁ በተጨማሪም ለእናንተ መልካም የሆነውን ሁሉ ለማድረግ አብሯችሁ ሊሄድ ይችላል። ወኪላችሁ አብሯችሁ እንዳይሆን የሚያደርግ ምክንያት ካላችሁ ለሠራተኞቹ መናገር አለባችሁ።

በቃለ መጠይቁ መጀመሪያ፣ ቃለ መጠይቅ አድራጊውና ወኪላችሁ የቃለ መጠይቁን ሂደትና ያላችሁን መብቶች ያብራሩላችኋል። ያልገባችሁ ነገር **ካለ ወይም ሌሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባካችሁ ጠይቁ!**

ቃለ መጠይቁ መብታችሁና የማመልከቻችሁ ጠቃሚ አካል ነው።

ቃለ መጠይቁ በሚገባችሁ ቋንቋ ይደረጋል። የሚደረግበትን ቋንቋ መረዳት ካልቻላችሁ፣ መግባባት እድትችሉ አስተርጓሚ እዲመጣ መጠየቅ ትችላላችሁ። አስተርጓሚው እናንተ የምትሉትንና ቃለ መጠይቅ አድራጊው የሚናገረውን ብቻ ይተረጉማል። አስተርጓሚው የራሱን/የራሷን የግል አመለካት አይጨምርም/አትጨምርም። አስተርጓሚውን ለመረዳት ችግር ካጋጠማችሁ ልትነግሩን ይገባል እና/ወይም ወኪላችሁን አናግሩ።

ቃለ መጠይቁ በሚስጥር ይያዛል። ይህም ማለት ከምትሰጡት መረጃ ውስጥ የትኛውም መረጃ፣ ለጥገኝነት ማመልከታችሁን ጨምሮ፣ የመጣችሁበት አገር ውስጥ የሚገኙ የቤተሰብ አባላት ወይም እናንተ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ለሚችሉ የመጣችሁበት አገር ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች ወይም ባለ ስልጣናት አይላክም።

እናንተና ጠበቃችሁ ስለዱብሊን አሠራር የጊዜ ሰሌዳ ግንዛቤ ያላችሁ መሆኑ ጠቃሚ ነው።

ወደ ሌላ አገር መሄድ እንደሚኖርባችሁ ወይም እዚሁ መቆየት እደምትችሉ ለማወቅ ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል?

ማመልከቻችሁን ለመመርመር ሀላፊነት የሚወስደው ሌለ አገር ሆኖ ቢገኝስ?

→ በዱብሊን አገር ውስጥ ጥገኝነት ስትጠይቁ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያችሁ ከሆነ ወደ ሌላ አገር ትላካላችሁ ምክንያቱም እናታችሁ፣ አባታችሁ፣ ወንድማችሁ፣ እህታችሁ፣ አክስታችሁ፣ አጎታችሁ፣ ወንድ አያታችሁ ወይም ሴት አያታችሁ በዚያ አገር ካሉ የጥገኝነት ጥያቄያችሁ እስኪመረመር ወደዚያው ሄዳችሁ ከእሱ/እሷ/እነሱ ጋር አንድ ላይ መቆየት ትችላላችሁ።[4]

→ እዚህ አገር ላይ የጥገኝነት ጥያቄ ከላስገባችሁ ሆኖም በፊት በሌላ የዱብሊን አገር ውስጥ የጥገኝነት ጥያቄ አስገብታችሁ ከሆነ፣ እዚያ ያሉት ሠራተኞች የጥገኝነት ጥያቄያችሁን እንዲያዩት ወደዚያ ተመልሳችሁ ልትላኩ ትችላላችሁ።[5]

በሁለቱም ሁኔታዎች፣ የጥገንነት ጥያቄ ከጠየቃችሁበት ጊዜ ጀምሮም ይሁን በሌላ የዱብሊን አገር ጥገኝነት መጠየቃችሁን ካወቅንበት ጊዜ ጀምሮ፣ እናንተን ወደሌላ አገር ለማዛወር ለመወሰን እስከ አምስት ወራት ሊወስድ ይችላል። ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ሠራተኞቹ በተቻለ ፍጥነት ስለ ውሳኔው ያሳውቋችኋል።

→ እዚህ አገር ላይ የጥገኝነት ጥያቄ ካላቀረባችሁና ከዚህ በፊት በሌላ አገር ላይ ያቀረባችሁት የጥገኝት ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ ተመርምሮ ውድቅ ከተደረገ፣ ያኛውን አገር መልሶ እዲወስዳችሁ ወይም ወደ መጣችሁበት አገር ወይም ወደ ቋሚ መኖሪያችሁ ወይም ደህና ወደሆነ ሦስተኛ አገር መልሶ ወደ መላክ እንዲሄድ ልንጠይቅ እንችላን።

የጥገኝት ጥያቄያችሁ የሌላ አገር ሀላፊነት ነው ብለን ከወሰንን፣ ሀላፊነቱን እንዲወስድ የተጠየቀው አገር ጥያቄውን ሲቀበለው፣ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረባችሁትን ጥያቄ እኛ እንደማንመረምር በምትኩ ሀላፊነቱን ወደወሰደው አገር እደምናዛውራችሁ ይነገራችኋል።

---

4) ይሄንንም ሰዎች “ሀላፊነት መውሰድ” ብለው ሲጠሩት ልትሰሙ ትችላላችሁ።
5) ይሄንንም ሰዎች “መልሶ መውሰድ” ብለው ሲጠሩት ልትሰሙ ትችላላችሁ።

ዝውውራችሁ የሚከናወነው ሌላኛው አገር ሀላፊነቱን በተቀበለ ወይም ውሳኔውን ከተቃወማችሁና ለመከራከር ከወሰናችሁ፣ ከይግባኙ ወይም ከግምገማው የመጨረሻ ውሳኔ ጀምሮ በስድስት ወራት ውስጥ ነው። (ይሄ ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራውን ከታች ያለውን ተመልከቱ!) ይሄ የጊዜ ገደብ ከታሰራችሁ እስከ አንድ ዓመት ወይም ከሸሻችሁና ከጠፋችሁ እስከ 18 ወራት ድረስ ሊራዘም ይችላል።



©iStockphoto / Joe Gough

ወደ ሌላ አገር መሄድ ካልፈለጋችሁ ምን ይፈጠራል?

ይሄን አስመልክቶ ከተወካያችሁ ጋር ተነጋሩ!

ማመልከቻችሁ እንዲመረመር ወደ ሌላ አገር እንድትዛወሩ ከወሰንና በዚህ ካልተስማማችሁ፣ የማዛወሩን ውሳኔ የመቃወም ዕድል አላችሁ። ይሄንን "ይግባኝ" ወይም "ከለሳ" እንለዋለን።

የማዛወር ውሳኔውን ከሠራተኞቹ ስትቀበሉ፣ ለሄሊሲንኪ አስተዳዳራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት 30 ቀናት አላችሁ። ይግባኙን በዚያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው። ተወካያችሁ በዚህ ጉዳይ ላይ ሊረዳችሁ ይገባል።

- ይግባኛችሁ እየታየ እያለ መዛወራችሁ እንዲቆይ ለመጠየቅ ሰባት (ቀናት) አላችሁ። ፍርድ ቤት ወይም ሸንጎ በዚህ ጥያቄ ላይ ውሳኔውን በፍጥነት ያሳልፋል። የማቆየት ጥያቄውን ውድቅ ካደረገ፣ ለምን እንደዚያ እንደተደረገ ምክንያት ይሰጣችኋል።
- በዚህ አገር ላይ በተላለፈ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የትኛውን ሠራተኛ ማግኘት እንዳለባችሁ ከዚህ ወረቀት ጀርባ መረጃ ታገኛላችሁ።

በዚህ የ"ይግባኝ" ሂደት ውስጥ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት፣ አስፈላጊ ከሆነም የቋንቋ ድጋፍ ይሰጣችኋል። የምትከፍሉት ገንዘብ ከሌላችሁ የነጻ የሕግ ድጋፍ መጠየቅ ትችላላችሁ፡ ፡ የዚህ ወረቀት ጀርባ ይግባኛችሁ ላይ ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ የሕግ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶች ዝርዝር ይዟል።

ማረፊያ ቤት መቆየት

ወደሚፈልጉበት ቦታ መጓጓዝ የማይችሉና ለቀው ሊወጡ የማይችሉት የተዘጋ ሕንጻ ውስጥ ባለ ቤት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች “ማረፊያ ቤት” የሚቆዩ ይባላሉ።

ብቻችሁን ያላችሁ ለአቅመ አዳም ያልደረሳችሁ ልጆች ከሆናችሁ ሲመሽ ወይም ውጪ ሲጨልም ቤት ውስጥ መቆየት እንደሚኖርባችሁ የሚያደርጉ ሕጎች ባሉበት ቤት ውስጥ ወይም ወደ ውጭ ልትወጡ ከሆነ ልትወጡ እንደሆነና የምትመለሱበትን ሰዓት ለሚንከባከቧችሁ ሰዎች ማሳወቅ እንዲኖርባችሁ የሚያደርጉ ሕጎች ባሉበት ቤት ውስጥ መቆየት ትችላላችሁ። እነኚህ ሕጎች የእናንተን ደሕንነት ለመጠበቅ ይጠቅማሉ። ይሄ ማረፊያ ቤት ውስጥ ናችሁ ማለት አይደለም።

ሕጻናት በፍጹም ማለት ይቻላል ማረፊያ ቤት ውስጥ እንዲቆዩ አይደረግም።

ማረፊያ ቤት ውስጥ ናችሁ? ማረፊያ ቤት ውስጥ ስለመሆናችሁ እርግጠኛ ካልሆናችሁ እባካችሁ በተቻለ ፍጥነት ተወካያችሁን፣ የሕግ አማካሪያችሁን[6] ወይም ሠራተኞቹን ጠይቁ። ያኔ ስላላችሁበት ሁኔታ ልታዋሯቸውና ማረፊያ ቤት ውስጥ ከሆናችሁ የማረፊያ ቤት ውሳኔውን ልታቀወሙ ስለምትችሉበት ዕድል ልታናግሯቸው ትችላላችሁ።

ራሳችሁን ማረፊያ ቤት ልታገኙበት የምትችሉበት ዕድል አለ። ብዙውን ጊዜ፣ ይሄ የሚከሰተው የመንግስት ሠራተኞቹ ከ18 ዓመት በታች መሆናችሁን ካላመኑበትና ወደ ሌላ አገር መላክን ስለምትፈሩ ከእነሱ ትሸሻላችሁ ወይም ትደበቃላችሁ ብለው ካመኑ ነው።

ለምን በማረፊያ ቤት እንድትቆዩ እንደተደረገና በማረፊያ ቤት እንድትቆዩ የተደረገበትን ውሳኔ እንዴት መቃወም እንደምትችሉ በጽሑፍ ማብራሪያ የማግኘት መብት አላችሁ። የማረፊያ ቤት ውሳኔውን ለመቃወም ከፈለጋችሁ የሕግ ድጋፍ የማግኘት መብት አላችሁ፣ ስለዚህ ካልተደሰታችሁ ለተወካያችሁ ወይም ለሕግ አማካሪያችሁ ተናገሩ።

6) በሕግ ፊት የእናንተን ጥቅም ለማስጠበቅ በሠራተኞቹ የታወቀ ሰው ነው። የሚያስፈልጋችሁ ከሆነ ተወካያችሁ እና/ወይም ሠራተኞቹ ይነግሯችኋል ሆኖም እናንተን ወክለው እንዲያመጡላችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ። የሕግ ውክልና ሊሰጧችሁ የሚችሉ ድርጅቶችን ለማግኘት የዚህን ወረቀት ጀርባ ተመልከቱ።

በዱብሊን አሠራር ወቅት በማረፊያ ቤት እንድትቆዩ ከተደረገ፣ ለሂደቱ የሚኖራችሁ የጊዜ ሰሌዳ እንደሚከተለው ይሆናል፡ የጥገኝነት ጥያቄያችሁን ባስገባችሁ **በአንድ ወር** ጊዜ ውስጥ ሌላ አገር የእናንተን ሀላፊነት እዲወስድ እንጠይቃለን። የተጠየቀው አገር ከዚያ በኋላ **በሁለት ሳምንት** ውስጥ መልስ መስጠት አለበት። በመጨረሻም፣ በማረፊያ ቤት ከቆያችሁ፣ ሀላፊነቱን የሚወስደው አገር ጥያቄውን በተቀበለ **በስድስት ሳምንት** ውስጥ ዝውውራችሁ ይደረጋል።

በማረፊያ ቤት እያላችሁ የማረፊያ ቤት ውሳኔውን ለመቃወም ካሰባችሁ፣ የመንግስት ሠራተኞቹ እናንተን በስድስት ሳምንት ውስጥ የማዛወር ሀላፊነት የለባቸውም። ከዚያም የመንግስት ሠራተኞቹ ስለሚኖራችሁ አማራጮች ያሳውቋችኋል።

የመንግስት ሰራተኞቹ ሌላ አገር የእናንተን ሀላፊነት እንዲወስድ መጠየቅባለባቸው ጊኤ ውስጥ ካልጠየቁ ወይም ዝውውራችሁን በሰዓቱ ካላደረጉ፣ በዱብሊን ድንጋጌ ውስጥ እናንተንለማዛወር አገልግሎት ማረፊያ ቤት መቆየታችሁ ያቆማል። እንደዚያ ከሆነ፣ በገጽ 11 የተቀመጡት መደበኛ የጊዜ ገደቦች ተግባራዊ ይሆናሉ።



©European Union



©European Union

የእናንተን ሀላፊነት ማን እደሚወስድ በምንወስንበት ጊዜ ውስጥ ያሏችሁ መብቶች ምንድን ናቸው?

የጥገኝነት ጥያቄዎን ለመመርመር ሀላፊነቱን እኛ ከወሰድን፣ ወይም ደግሞ ሌላ አገር ሀላፊነቱን የሚወስድ ከሆነ ወደዚያ እስከሚዛወሩ ድረስ እዚህ አገር ውስጥ የመቆየት መብት አለዎት። አሁን ያላችሁበት አገር የጥገኝነት ጥያቄያችሁን ለመመርመር ሀላፊነቱን ከወሰደ፣ በጥገኝነት ጥያቄያችሁ ላይ ቢያንስ የመጀመሪያ ውሳኔ እስኪተላለፍ ድረስ እዚህ የመቆየት መብት አላችሁ። መጠለያ፣ ምግብ ወዘተ የመሳሰሉትን ጥቅማ ጥቅሞች በተጨማሪም መሠረታዊ የጤና ሽፋንና የአደጋ ጊዜ የሕክምና ድጋፍ የማግኘት መብትም አላችሁ። የመማር መብት አላችሁ።

ስለ ሁኔታዎና በዱብሊን አገሮች ውስጥ ቤተሰብ ያለዎት ስለመሆኑ በአፍ ወይም በጽሑፍ መረጃ እንዲሰጡን ይሄንንም ሲያደርጉ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎትን ወይም ሌላ በደንብ የሚናገሩትን ቋንቋ እንዲጠቀሙ (ካስፈለገም አስተርጓሚ እንዲያገኙ) እድሉ ይሰጥዎታል፡ ፡ ወደሌላ አገር እንድትዛወሩ የተወሰነውን ውሳኔ በጽሑፍ እንዲደርሳችሁም ይደረጋል፡ ፡ እኛን ለበለጠ መረጃ እና/ወይም እዚህ አገር ያለውን የተባሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ቢሮን (UNHCR) የማግኘት መብት አላችሁ።

ስለ መብቶቻችሁ ተወካያችሁ እና የመንግስ ሠራተኞቹ የበለጠ ያብራሩላችኋል!

የምትሰጡት የግል መረጃ ዕጣ ፋንታ ምን ይሆናል? ለመጥፎ ዓላማ ጥቅም ላይ እደማይውል እንዴት ማወቅ ትችላላችሁ?

በዱብሊን አሠራ ወቅት የዱብሊን አገሮች ሠራተኞች በዱብሊን አሠራር ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት ዓላማ ብቻ እናንተ የምትሰጡትን መረጃ መለዋወጥ ይችላሉ።

ክፍት እንዲሆንላችሁ መብት የሚኖራችሁ፡

- ከእናተ ጋር ተያያዥ ለሆነ መረጃ። እንዲህ አይነቱን መረጃ ትክክል ካልሆነ ሊስተካል የሚገባው የዩሮዳክ መረጃን ወይም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ከዋሉ እዲሰረዙ ጭምር የመጠየቅ መብት አላችሁ።
- የዩሮዳክ መረጃዎችን ጨምሮ መረጃዎቻችሁ መስተካላቸውን ወይም መሰረዛቸውን ስለመጠየቅ የሚያብራራው መረጃ። ይሄም ለእናንተ የዱብሊን አሠራር ሀላፊነቱን የሚወስዱ ብቁ ባለሙያዎችን እና የግል መረጃ ጥበቃን አስመልክቶ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የሚያስተናግዱ የብሔራዊ የመረጃ ጥበቃ ሠራኞችን ያካትታል።

እርዳታ የት ማግኘት ትችላላችሁ

የጥገኝነት ባለስልጣኑ የመገኛ ዝርዝሮች
Maahanmuuttovirasto (የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት)
PL 10, 00086
Maahanmuuttovirasto
+ 358 295 419 600
www.migri.fi

ብቻውን ለሆነ ለአቅመ አዳም ላልደረሰ ልጅ ወኪል
ብቻውን ሆኖ ጥገኝነት ለሚጠይቅ ዕድሜው ለአቅመ አዳም ላልደረሰ ልጅ የአካባቢው ፍርድ ቤት ተወካይ ይሰይማል። የእንግዳ መቀበያ ማዕከሉ የተወካይ መጠየቂያ ማመልከቻ ለአካባቢው ፍርድ ቤት ያስገባል።

የሕጻናት ጥበቃ
የእንግዳ መቀበያ ማዕከሉ ለጉዳዩ በተመደበው የማሕበራዊ ሠራተኛ ለሕጻኑ ጤና እና እድገት ጠቃሚ ናቸው የሚባሉ ሁሉንም የማሕበራዊ ደሕንነት አገልግሎቶች የማሟላት ግዴታ አለበት። ጥያቄ ካላችሁ በእግዶች መቀበያ ማዕከሉ ያለውን/ያለችውን የማሕበራዊ ሠራተኛ አነጋግሩ።

ለዱብሊን አሠራር ሀላፊነቱን የሚወስደው ሠራተኛ
የፊንላድ የስደተኞች አገልግት (Maahanmuuttovirasto)
ከላይ የተጠቀሱት የማግኛ ዝርዝሮች።

የብሔራዊ ማስተባበሪያ ቢሮ (የመረጃ ጥበቃ)
Tietosuojavaltuutetun toimisto
(የመረጃ ጥበቃ የእንባ ጠባቂ ቢሮ)
PL 800, 00521 Helsinki
+ 358 295 666 700
የስልክ መመርያ:
+358 295 666 777
ሰኞ–አርብ በ 9–11
tietosuoja@om.fi
www.tietosuoja.fi

የዩሮዳክ ተቆጣጣሪ ማንነትና ወኪሉ/ወኪሏ
የመገኛ ቦታዎች፡ ብሔራዊ ፖሊስ ቦርድ (Poliisihallitus) እና የፊንላድ የስደተኞች አገልግሎት (Maahanmuuttovirasto)

የተቆጣጣሪው ቢሮ የመገኛ ዝርዝሮች
+ 358 295 480 181
Poliisihallitus (ብሔራዊ የፖሊስ ቦርድ)
PL 22, 00521 Helsinki
kirjaamo.poliisihallitus@poliisi.fi

Maahanmuuttovirasto (የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት)
PL 10, 00086
Maahanmuuttovirasto
+358 295 419 600
www.migri.fi

በዩሮዳክ ስርዓት ውስጥ የተመዘገበ ከእናንተ ጋር የሚያያዝ መረጃ ለማየት ከፈጋችሁ፣ ፖሊስ ጣቢያ በአካል ቀርባችሁ ጥያቄ አስገቡ። ማንነታችሁን የሚያረጋግጥ ነገር ለማሳየት ተዘጋጁ። ግንኙነትዎን የጥገኝነት ጥያቄዎን ከተረከበው የፖሊስ አገልግሎት ቦታ ጋር እንድታደርጉ እንመክራለን። የፖሊስ አገልግሎት ቦታ የመገኛ መረጃ በpoliisi.fi ላይ ይገኛል።

Suomen Punainen Risti (የፊንላንድ ቀይ መስቀል)
Tehtaankatu 1 a
00140 Helsinki
+358 20 701 2000
info@redcross.fi
www.redcross.fi

የጠፉ የቤተሰብ አባላትን ፈልጉ።

የሕግ ድጋፍ ቢሮና የስደተኞች ድጋፍ ድርጅቶች
የህግ ድጋፍ በሕግ ድጋፍ ቢሮዎችና በሌሎች የሕግ ቢሮዎች እንዲሁም ለጥገኝነት ጠያቂዎች የሕግ አገልግሎት እንደሚሰጡ ለእንግዶች መቀበያ ማዕከሉ ፈቃደኝነታቸውን ባሳወቁ ጠበቃዎች ይሰጣል። የሕግ ድጋፍን አስመልቶ የበለጠ መረጃ ከፈለጋችሁ የእንግዶች መቀበያ ማዕከል ሠራተኛውን አናግሩ።

የአለማቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ዝርዝር መገናኛ የሀገር ፅህፈት ቤት ፊንላንድ
IOM Finland
Unioninkatu 13, 6ኛ ፎቅ
PL 851, 00101 Helsinki
+358 9 684 1150
fiavrrcases@iom.int
www.iom.fi

በፈቃዳችሁ ወደመጣችሁት አገር መመለስ ከፈለጋችሁ፣ የእንግዳ መቀበያ ማዕከሉን በማነጋገር ምክር ጠይቁ።

የተባሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ቅርቡ አካባቢያዊ ቢሮ
UNHCR
Sveavägen 166, 15th floor
SE-11346 Stockholm
SWEDEN
Tel. +46 10 10 12 800
swest@unhcr.org

European Commission

Maahanmuuttovirasto
Migrationsverket
Finnish Immigration Service

POLIISI
POLISEN I FINLAND
Police of Finland

Rajavartiolaitos
Gränsbevakningsväsendet
The Finnish Border Guard

12.8.2019 - amhara